THOMSON REUTERS FOUNDATION

28 TOO MANY
FGM... let's end it.

ORCHID PROJECT




# የሴት ልጅ ግርዛት እና ህጉ በኢትዮጵያ

**ሀምሌ 2010 ዓ.ም**

## በኢትዮጵያ እድሜያቸው ከ 15-49 ከሆኑት ሴቶች መካከል 65.2% የሚሆኑት ሴቶች ለሴት ልጅ ግርዛት የተጋለጡ ናቸው።

104.5 ሚሊዮን የሚጠጋ የህዝብ ብዛትን ይዛ፣ ኢትዮጵያ በአጠቃላይ የሴት ልጅ ግርዛት በተፈፀመባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ቁጥር ከግብፅ ቀጥሎ ሁለተኛ ናት።

ለችግሩ በከፍተኛ ደረጃ ተጋለጭ የሆኑት ክልሎች ሚገኙት በሀገሪቱ ምስራቃዊ ክፍል ነው።




**የሴት ልጅ ግርዛት በክልል መስፋፋት**

*[የመረጃ ምንጭ ስነሕዝብ እና ጤና ጥናት 2016]* © 28 Too Many

- ከ15-40 እድሜ ካላቸው ከተገረዙ እናቶች የተወለዱ ሴት ልጆች መካከል 64% እድሜያቸው አራት አመት ሳይሞላ ተገርዘዋል።
- ‘መቁረጥ፣ የተወሰነውን ስጋ ማስወገድ’ የተለመደ የሴት ልጅ ግርዛት አይነት ነው።
- በአብዛኛው ሁሉም የሴት ልጅ ግርዛቶች የሚከናወኑት ‘በባህላዊ ገራዦች’ ነው።

Source of data: Central Statistical Agency (CSA) [Ethiopia] and ICF (2016) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2016: Key Indicators Report*. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA. CSA and ICF. Available at **https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR328/FR328.pdf**.

*For further information on FGM in Ethiopia, see* ***https://www.28toomany.org/ethiopia/***.

# ሀገራዊ የህግ ማዕቀፎች

| የኢትዮጵያ ሀገራዊ የህግ ማዕቀፎች እይታ | |
|---|---|
| | |
| *ህገ መንግስቱ በግልፅ የሚከለክላቸው:-* | |
| X | በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ ጥቃት ማድረስ |
| ✓ | ጎጅ ድርጊቶችን መፈፀም |
| X | የሴት ልጅ ብልትን መቁረጥ |
| | |
| *ብሄራዊ ህጉ:-* | |
| X | ለሴት ልጅ ግርዛት ግልፅ የሆነ ትርጓሜ ሰጥቶታል |
| ✓ | የሴት ልጅ ግርዛት ማከናወን ወንጀል እንደሆነ ይገልፃል |
| ✓ | የሴት ልጅ ግርዛት እንዲፈፀም ቁሳቁስ ማቅረብ፣ ማመቻቸት እና/ወይንም መርዳት ወንጀል እንደሆነ ይገልፃል |
| X* | የሴት ልጅ ግርዛት ሲከናወን ሪፖርት አለማድረግ ወንጀል እንደሆነ ይገልፃል |
| X* | የጤና ባለሙያዎች በሴት ልጅ ግርዛት መሳተፍ ወንጀል እንደሆነ ይገልፃል |
| X* | ድንበር ተሻጋሪ የሴት ልጅ ግርዛት ማከናወን ወንጀል እንደሆነ ይገልፃል |
| | |
| ✓ | **መንግሥት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም ስትራቴጅ አስቀምጧል** |

** ወንጀል መሆኑ ተለይቶ አልተቀመጠም፤ ጥቃቶች በብሄራዊ ህጉ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ነው የተገለፁት (ከታች ያለውን ይመልከቱ)።*

## የሴት ልጅ ግርዛትን የሚከለክል ምን ህግ አለ?

በኢትዮጵያ ተፈርሞ የፀደቀው የአለማቀፍ እና ክልላዊ ስምምነቶች አጠቃላይ ምልከታ ከዚህ ሪፖርት ጋር በተጨማሪ መግለጫነት ተያይዞ ይገኛል፡ኢትዮጵያ በመጠኑ የእስልምና እና የተለምዶ ህግጋት ያሉበት የፍትሐ ብሔር ህግ ስርዓት አላት፤ የፍትሐ ብሔር ስነ-ስርዓት ህጉም የእንግሊዝ የጋራ ህግ መርሆዎች ተፅዕኖ ያለበት ነው።

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ህገ መንግስት (እንደ ኢትዮጵያዉያን አቆጣጠር በ1987/እንደ አዉሮፓዊያን አቆጣጠር በ1995)**[1] ስለ ሴት ልጅ ግርዛት በቀጥታ አይጠቅስም፤ ነገር ግን ድርጊቱን በተመለከተ ጠቃሚ ሌሎች ህግጋቶችን ይዟል:-

- **አንቀፅ 16** ሁሉም ዜጎች “አካላዊ ጉዳት” እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።
- **አንቀፅ 18(1)** “ሁሉም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ሰብአዊነት ከጎደለው ወይንም ከሚያዋርደ አያያዝ ወይንም ቅጣት ከለላ የማግኘት መብት አለው” በማለት ይገልፃል።

- **አንቀፅ 25** " የእኩልነት መብትን " ይመለከታል።
- **አንቀፅ 35** " የሴቶችን መብት " ይመለከታል።
- **አንቀፅ 35 (4)** "መንግስት የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ተፅዕኖ በማስወገድ የሴቶችን መብት ማስከበር አለበት። ህጎች፣ ልማዶች እና ጨቋኝ ወይም በሴቶች ላይ አካላዊም ይሁን አዕምሯዊ ጉዳት የሚያስከትሉ ድርጊቶች የተከለከሉ ናቸው።" በማለት ይገልፃል።
- **አንቀፅ 36** "የህፃናት መብትን" ሲተነትን ሁሉም ድርጊቶች "የህፃናትን ጥቅም እና ፍላጎት ያማከሉ መሆን አለባቸው" በማለት ይገልፃል።

ኢትዮጵያ የየራሳቸው ህገመንግስት ያላቸው ዘጠኝ ክልላዊ መንግስታት አሏት። እነዚህ ህገመንግስቶች በይዘታቸው አብዛኞቹ ተመሳሳይ ሲሆኑ የሰብዓዊ መብት አያያዝን በተመለከተም ቢሆን አብዛኞቹ ተቀራቢ ሲሆኑ ፤ አንዳንዴ ከፌደራል ህገመንግስቱ ጋር አንድ አይነት ናቸው[2]። በአጠቃላይ እነዚህ የሰብዓዊ መብት ህግጋቶችን ለሴት ልጅ ግርዛት እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ጠቂሚ ሲሆኑ ይችላሉ ። ለምሳሌ **በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይንም አካላዊም ይሁን አዕምሯዊ ጉዳት የሚያስከትሉ** ተግባራትን በመከልከል የፌደራል ህገመንግስቱን ይዘት ያንፀባርቃል[3]።

**በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛትን በዋነኝነት የሚመለከተው ህግ አዋጅ ቁ. 414/2004፣ ወይንም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ ነው[4] ። ይህ የፌደራሉ ህግ በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት መፈፀም ወይንም እንዲፈፀም ማድረግ የወንጀል ድርጊት** አድርጎ **ይደነግጋል ።**

ማንኛዉም ድርጊት አካላዊ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ከወጀለኛ ህጉ በተጨማሪ በፍትሐ -ብሔር ህግ (1960) ያስቀጣል[5]።

## ሕጉ ምንን ያጠቃልላል

**በወንጀልህግ ምዕራፍ 3 አንቅጽ 561- 570፤** 'በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካኝነት በህይወት፣ በአካል እና በጤና ላይ ጉዳት በማድረስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች' ተገልፀዋል። እነኚህ ህጎች የሴት ልጅ ግርዛትን በኢትዮጵያ ቢከለክሉም፣ ስለድርጊቱ ግን ግልፅ የሆነ ትርጉም አይሰጡም።

የወንጀልህጉ በተለይም የሚከተሉትን ጥሰቶች ይጠቅሳል፡-

- **አንቀጽ 561 እና 562፥** በህክምናው አለም በጎጂነታቸው የታወቁ ባህላዊ ስርዐቶችን በመፈጸም ምክኒያት የነፍሰ ጡር ሴቶችንም ሆነ፣ አዲስ የተወለዱ ጨቅላ ህጻናት ህይወትን አደጋ ላይ ስለመጣል፣ እንዲሁም የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ስለማድረስ ያትታሉ።
- **አንቀጽ 565 እና 566፥** በተከታታይ በየትኛውም እድሜ ላይ ባለች ሴት ላይ ግርዛት መፈጸም፣ እንዲሁም የሴት ልጅ ብልት መስፋት የሚያስከትሏቸውን ቅጣት ያሰፍራሉ።
- **አንቀጽ 568 ፥** በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሽታን ማስተላለፋ የሚያሰቀጣ መሆናቸዉን ያሰፍራል።
- **አንቀጽ 569 እና 570፥** በሴት ልጅ ግርዛት ተካፋይ የሆነ ወላጅ ወይም ሌላ ሶስተኛ ሰዉ እንዲሁም ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን (የሴት ልጅ ግርዛትን) የሚከለክሉ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችን እንደይፈጸሙ በይፋም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያነሳሳ ወይም የቀሰቀሰ ይህን አይነት አላማ ለማስፈጸም ህዝብን ያደራጀ፣ ለዚህ አላማ

በተደራጀ እንቅስቃሴ ያሳተፈ ወይም ለዚህ አላማ ድጋፍ የሰጠ ማንኛዉም ሰዉ በወንጀል ጥፋተኛ ተደርጎ ሊቀጣ እንደሚችል ይሸፍናሉ።

በወንጀልህጉ የሴት ልጅ ግርዛት ተፈጽሞም ሆነ ታቅዶ ባለበት ሁኔታ ለተገቢው አካል አለማሳወቅ እንደወንጀል አልተጠቀሰም። ሆኖም ግን፤ **አንቀጽ 443** በስሩ ጠቅለል አድርጎ አንዳንድ ልዩ ወንጀሎችን ለሚገባው አካል አለማሳወቅ የሚያስከትለውን ቅጣት አስፍሯል [ከታች ይመልከቱ]። በተጨማሪም፣ ይህ የኢትዮጵያ ወንጀል ህግ፣ ያልተገረዘች ሴትን እና ቤተሰቦቿን ከማህበረሰቡ ለሚደርስባቸው የመዋረድ እና የመገለል ጫና፣ እንደኬንያ እና ዩጋንዳ ያሉ ሌሎች የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በህጋቸው ውስጥ እንዳሰፈሩት የህግ ከለላ አያደርግም።

እንደሴቶች ግርዛት የመሳሰሉትን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ፈፃሚ ባለሙያዎች ያላቸውን ሀላፊነት በተመለከተ፣ የፍትሀ ብሄር ህግ **አንቀጽ 2067[1]** ላይ ያለው ቅጣት ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችላል። በዚህ አንቀጽ መርህ መሰረት፣ 'አንድ ሰው በሰራው ስራ በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ተጠያቂ ነው።' ስለዚህም የሴት ልጅ ግርዛት ተጠቂ የሆኑ ግለሰቦች፣ ከወንጀለኞቹ ካሳ የመጠየቅ መብት አላቸው።

### *በህክምና የታገዘ የሴት ልጅ ግርዛት*

የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያትቱት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በህክምና የታገዘ ግርዛት እዚህ ግባ የማይባል እንደሆነ ነው። እድሜያቸው ከ15-49 ከሆኑ ሴቶች 1% የሚያህሉ ብቻ ሲሆኑ በጤና ባለሙያዎች አገልግሎቱን የሚያገኙት፤ ከ0-14 ዓመት እድሜ ያሉ ሴቶች ላይ ግን በመጠኑ ከፍ ያለ 1.9% ተመዝግቧል[6]። ከዚህ ቀደም የቀረቡ ጥናቶች፣ በአንዳደንድ ከተሞች ከ10% በላይ እንዲሁም በአዲስ አበባ ውስጥ እስከ 20% እንደሚደርስ ጠቅሰዋል[7]።

ይህ በጤና ባለሙያዎች የሚደረግ ግርዛት በወንጀልህጉ ላይ በተለየ ሁኔታ ባይጠቀስም፣ **ከ561-570** ባለው ሰፊ ወሰን፣ በአለምአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ሁሉንም ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ፈጻሚ አካላትን የሚያወግዝ በመሆኑ፣ የህክምና ባለሙያዎችንም ማጠቃለሉ አይቀሬ ነው። ይህ ህግ ግርዛትን የሚደግፍ ወይም የሚያበረታታ የህክምና ባለሙያንም ጭምር በህግ ተጠያቂ ያደርጋል።

### *ድንበር አቋራጭ የሴት ልጅ ግርዛት*

አንዳንድ ሃገራት የሴት ልጅ ግርዛትን ወንጀለኝነት ቢደነግጉም፣ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ግን በየሰፈሮች ጉራንጉር ወይም በተቃራኒ ድንበር ክልል ውስጥ ድርጊቱ መከናወኑ አልቀረም። ኢትዮጵያም፤ የተለያዩ ህጎች እና አፈጻጸሞች ባሏቸው ፣እንደ ኬንያ ካሉ የሴት ልጅ ግርዛት ላይ ያሏቸው ህጎች ጠቅለል እና ለቀቅ ባሉ፣ እንዲሁም እንደ ሶማልያ ባሉ በጉዳዩ ላይ ምንም ስራ ላይ የዋሉ ህጎች በሌላቸው ሀገራት ትዋሰናለች።

ይህ ለግርዛት ሲባል የሚደረግ የቤተሰብ ስደት፣ በአሁን ሰዐት ጎጂ ባህሉን ለማስቆም ባለው ንቅናቄ ላይ ትልቅ እክል ፈጥሯል። የኢትዮጵያ ህግ ይህንን ጉዳይ ለይቶ ባያሰፍረውም፣ የወንጀልህጉ ላይ ከ**አንቀጽ 11-22** ፥ በሌላ ሃገር ዜጎች ሃገሪቷ ውስጥ እና በኢትዮጵያዊ ዜጎች ከሃገሪቷ ውጪ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ያተኩራል።

በተለይም **አንቀጽ 11[1]** ፥ 'አንድ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጪ ሃገር ዜጋ፤ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በዚህ ህግ ከተመለከቱት ወንጀሎች ማናቸውንም ቢያደርግ ይህ ህግ ተፈጻሚ ይሆንበታል።'

**አንቀጽ 18[1] [ለ]** ፥ 'ማንኛውም ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ፣ ወይም ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ከኢትዮጵያ ውጪ ከዚህ በላይ በተመለከቱት አንቀጾች ከተገለጹት ወንጀሎች ሌላ የፈጸመ እንደሆነ፣ አድራጊው በዚሁ ወንጀሉ በወጪ ሃገር ሳይከሰስ ከቀረ፣ ይህ የወንጀል ህግ በምትክነት ተፈጻሚ የሚሆነው፣ በተፈጸመው ወንጀል ከባድነት በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ተከሳሹ ተይዞ ተላልፎ እንዲሰጥ ለማድረግ በቂ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው።'

## ቅጣቶች

የወንጀልህጉ እነዚህን ቅጣቶች ያስቀምጣል፦

- **አንቀጽ 565** ፡ 'ማንም ሰው በየትኛውም የዕድሜ ክልል የምትገኝን ሴት የገረዘ እንደሆነ፣ ከ3 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከ500 ብር በማያንስ መቀጮ ይቀጣል (18ዶላር USD[8]) ።
- **አንቀጽ 566[1]** ፡ 'ማንም ሰው የአንዲትን ሴት ብልት የሰፋ እንደሆነ፣ ከ3-5 ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል።'
- **አንቀጽ 566[2]** ፡ 'በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ድርጊት የአካል ወይም የጤና ጉዳት ደርሶ እንደሆነ፣ በወንጀለኛ ህጉ ከፍተኛ ቅጣት የሚጥል ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቅጣቱ ከ5-10 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።'
- **አንቀጽ 569**፡ 'በዚህ ምዕራፍ ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ ተካፋይ የሆነ ወላጅ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው፣ ከ3 ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ500 (18ዶላር USD) ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።'
- **አንቀጽ 570**፡ 'ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ የዚህ ህግ ድንጋጌዎች እንዳይፈጸሙ በይፋም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያነሳሳ ወይም የቀሰቀሰ፣ ይህን አይነት አላማ ለማስፈጸም ህዝብን ያደራጀ፣ ለዚህ ዓላማ በተደራጀ እንቅስቃሴ ያሳተፈ፣ ወይም ለዚህ ዓላማ ድጋፍ የሰጠ ማንኛውም ሰው ከ3 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከ500 (18ዶላር USD) ብር በማያንስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።'

[በ2004ቱ የወንጀልህግ ላይ የተጠቀሱት የገንዘብ ቅጣቶች ከዚያን ጊዜ ወዲህ ያለ የጉዳዩ መበራከትን በማካተት የታደሱ አይደሉም፤ ስለዚህም የህግጋቶቹ ላይ የሰፈሩትን ቅጣቶች ክብደት አቅልሎታል።]

ወንጀሎችን ለተገቢው አካል ማመልከትን በተመለከተ፣ **አንቀጽ 443[1] [U]** ፡ 'ማንም ሰው በቂ ምክኒያት ሳይኖረው በሞት ወይም በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል መፈጸሙን፣ ወይም የወንጀለኛውን ማንነት እያወቀ ለሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ፣ ከብር 1000 (36ዶላር USD) በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ6 ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት' እንደሚቀጣ ያሰፍራል።

# የህግ ተፈጻሚነት

## ችሎት

አለፍ አለፍ ብሎ ስለህጉ ተፈጻሚነት እና ስለሴት ልጅ ግርዛት ክሶች ሪፖርቶች ቢኖሩም፣ ስለእነዚህ ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማግኘት ግን ለብዙሃኑ የሚቻል አይደለም። ለምሳሌ፦ በ2012 አንድ ገራዥ እና የ6 ሴት ልጆች ወላጆች ተከሰው፤ ገራዡ የ6 ወር እስራት ሲፈረድበት፣ የልጆቹ ወላጆች ደግሞ የ500 (በጊዜዉ ከ27 ዶላር (USD) ጋር እኩል ነበር) ብር ቅጣት ተጥሎባቸው አልፏል። በ2011 እና 2010 እንደዚሁ አንድ፣ አንድ ክሶች ተመዝግበዋል[9]።

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የታሳሪዎች ቁጥር መጨመር ቢታይም፣ ህግ ማስፈጸም ላይ የሚታየው ድክመት ግን ፍርድ ቤቶች ጋር የሚደርሱት ክሶችን በጣም አናሳ ያደርጋቸዋል። በ2015 በየተባበሩት መንግስታት የህዝብ ፈንድ (UNFPA) እና በተባበሩት መንግስታት አለም አቀፍ የህጻናት አስቸኳይ ፈንድ ህብረት (UNICEF) የሴት ልጅ ግርዛትን (UNJP) ለማቆም የተደረገው የጋራ ፕሮግራም ጥናት

እንደሚያሳየው፣ በዚያ አመት ብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ በጠቅላላ ወደ 279 እስራቶች ቢመዘገቡም፣ ከእነዚህ ውስጥ ግን ጥፋተኛ የተባለዉ አንድ ብቻ መሆኑን ነው[10]። በድጋሚም በ2016 አንድ ሌላ የጥፋተኝነት ፍርድ ተመዝግቧል[11]።

## ወሳኝ የመንግስት አካላት እና እቅዶች

በሴቶች ግርዛት ላይ ያለው የኢትዮጵያ ብሄራዊ እቅድ ተግባራዊነት የሚመለከተው አካል የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚንስቴር ነው።

በ2013 ኢትዮጵያ በሴቶች እና ህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ባህላዊ ስርዓቶችን ለማስቀረት የተዋቀረው ብሄራዊ እቅድ እና የአሰራር ወርሀን የሚያስተባብር እና ስራ ላይ የሚያውል ብሄራዊ የተግባራዊነት እና ቁጥጥር መድረክ አቋቁማለች[12]። የዚህ እቅድ ቁልፍ ሃላፊነቶች በህብረተሰቡ ዘንድ በማህበረሰብ ተኮር ውይይቶችን በማካሄድ ፣ የትብብር ትስስሮችን በማዳበር፣ ለሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታን በማመቻቸት፣ ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት እና የጤና አገልግሎት የማግኘት እድልን ለማረጋገጥ የአገልግሎቶችን ትስስር በመፍጠር፣ እንዲሁም ከተለያዩ የዕምነት መሪዎች ጋር በመስራት ግንዛቤ መፍጠርን ያጠቃልላሉ።

በተለይም ህጉ ላይ የሴቶች እና ህጻናት ጥበቃዎች በተመለከተ የሚያትተው የብሄራዊ ዕቅዱ **ክፍል 3.2.2**፣ ዋና አላማው ብሄራዊ ፖሊሲውን እና ህጋዊ መዋቅሩን በተለያዩ ጣልቃ ገብ ስራዎች ማጠናከር እና ማሻሻል አድርጎ ቀርጿል። እነዚህም እንደ፡-

- የህግ እና የፖሊሲ መዋቅሩን ከአለም አቀፍ እና ክልላዊ ቁርጠኝነቶች ጋር አስታኮ በየጊዜው መገምገም፣
- በሁሉም የማህበረሰቡ አካላት በመታገዝ፣ ከፌዴራል እስከ አካባቢያዊ ያሉ ሲቪል እና ባህላዊ ህጎችን ማስታረቅ እና ማስማማት፤ ብሎም አፈጻጸማቸውን ማጠናከር፣
- አዳዲስ ፖሊሲዎችን እና ህጎችን አዲስ ለሚመጡ ሁኔታዎች እና ቁርጠኝነቶች ምላሽ ለመስጠት የሚችሉ እንዲሆኑ አድርጎ መቅረጽ፣
- ከፌዴራል አንስቶ እስከ አካባቢያዊ ያሉ ቁልፍ ተጫዋቾችን፣ እንዲሁም የማህበረሰብ ፖሊስ አካላትን አቅም ማጠናከር፣
- የፍትህ ስርዓቱ ቁልፍ ተጫዋቾችን ህግ ማስፈጸም ላይ ያካበቱትን ልምድ፣ በጎ አሰራር እንዲካፈሉ እና ለወደፊቱም እንዲያቅዱ አንድ ላይ ማሰባሰብ፣
- የህግ ተፈጻሚነትን ለማጠናከር እና ሴቶች እና ህጻናትን ለመጠበቅ እንዲረዳ፣ በሁሉም ተዋናዮች [የትምህርት እና ጤና ሴክተርን አካቶ] መካከል ያለውን ህብረት ማጠናከር፣
- ቴክኒካል ድጋፍን፣ ስልጠናዎችን ጨምሮ፣ ለሁሉም አካላት ማቅረብ፣
- የህግ ተፈጻሚነትን ለማሳደግ መጠይቆችን ማካሄድ እና የተገኙ መረጃዎችን በአግባቡ መጠቀም ያሉትን ይመስላሉ።

ከ2008 አንስቶ ከዩ.ኤን.ጄ.ፒ (UNJP) ጋር በትብብር እየሰራ ያለው የኢትዮጵያ አመራር፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጎጂ ልማዳዊ ስርዓቶችን ለማስወገድ የፀና በጀት አፅድቋል። በ2025 የሴት ልጅ ግርዛትን እና የልጆች ጋብቻን ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ የተያዘው እቅድ አካል በማድረግም፣ በ2013 የ10% የበጀት ምደባ ጭማሪ ለማድረግ መወሰኑ ይፋ ተደርጓል[13]።

# የሲቪል ማህበረሰብ ምልከታዎች

በብሄራዊ ስትራቴጂው፣ ኢትዮጵያ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና ከዩ.ኤን.ጄ.ፒ (UNJP) ጋር ባለው ትብብር የሴቶች ግርዛትን ለማስቆም ቆርጣ መነሳቷን እና መንግስቷም፤ ህግን በቀጥታ ተጭኖ ከማስከበር ይልቅ የባህሪ እና ማህበረሰባዊ ስርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ማተኮር መምረጡን ያለው ሁኔታ ያመላክታል። ለምሳሌ፡- ባለፉት 5 ዓመታት ማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሙያተኞች የተለያዩ ስልጠናዎች እና አቅም መገንቢያ ፕሮግራሞች ተበርክተዋል[14]።

በ2015 የኢትዮጵያ የአዋላጅ ነርሶች ማህበር ለ254 አዋላጅ ነርሶች የሴት ልጅ ግርዛትን ማስቀረት እንዲችሉ እና ከማህበረሰቡ ግርዛትን እንፈፅሙ ለሚደርስባቸው ጫና መቋቋም እንዲችሉ፣ የ2 ቀን ስልጠና ሰጥቷል[15]።

እንዲሁም፣ ኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመያዝ እና ወደህግ ለማቅረብ እንዲረዳ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥበቃዎችን ማጠናከር ላይ ትሰራለች። አሁን ያሉ መረጃዎች በመንግስት እና በሲቪል አካላት በሚደረገው እንቅስቃሴ ምላሽ እንዲሆን፣ በወጣት ሴቶች አካባቢ የድርጊቱን መቀነስ ይጠቁማሉ[16]።

ምንም እንኳን የሃገሪቷ ህጎች ቦታ ላይ ቢሆኑም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት የሚሰሩ አካላቶች ዘንድ ስለህጉ ያለው ዕውቀት እና የህጉ ተፈፃሚነት አሁንም ቢሆን ችግር ላይ እንደሆነ ይገለጻል። ስለህጉ ምንነት ያለው እውቀት በጎ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ውስጥ አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ሕጉን በማስፈጸም ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ተመራጭ ባለስልጣኖች ላይ ራሱ ቸልተኝነት ይታያል። ምንም ያህል የሴት ልጅ ግርዛት ሕገ-ወጥ ሆኖ ቢሰፍርም፣ አንዳንድ አካባቢያዊ የማህበረሰብ መሪዎች ባህላዊ የሴት ልጅ ግርዛት የሚፈጽሙ ግለሰቦችን ይደግፋሉ። ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ፣ በገጠር አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ከፖሊስና ከፍርድ ቤት ይልቅ ወደ ባህላዊ የፍትህ ተቋማት፤ ማለትም ወደ ሽምግልና ይሄዳሉ።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ የገጠር ቤተሰቦች ከህግ ተጠያቂነት ለማምለጥ፣ በከፍተኛ ሁኔታ በተደበቀ መልኩ የሴት ልጅ ግርዛትን ይፈጽማሉ። ይህ ደግሞ ሴቶችን ከፍተኛ ችግር ላይ ይጥላል (ለምሳሌ፡- ይህ ድርጊት አሳቻ በሆነ ጨለማ ቦታ እና ልምድ በሌላቸው ሰዎች ይሰራል) [17]። በዚህም ምክንያት የሴቶች አለመማር ወደፊት ለሚኖራቸው የህግና የመብት ዕውቀት ትልቅ እክል ይሆናል (በ2015 በግምት 41.1%)[18] ።

ምንም እንኳ ሚዲያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የህጉን ተግባራዊነት ውስንነት ቢገልጹም፤ በሚዲያ ነፃነት እና በሰብኣዊ መብት ዙሪያ ባሉ የሲቪል ማህበረሰቦች፣ የመንቀሳቀስ መብቶችና የጾታ እኩልነትን ማሰደግ ጨምሮ ያሉ ደንቦች ተግባራዊ ሆነው ይገኛሉ። እነዚህ ሁኔታዎች የመረጃ ተደራሽነትና ልውውጥን ውስን እንዲሆን ሲያደርጉ፣ ይህም በተራው የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት በሚሰራው ስራ ላይ የሚደረገውን የመረጃ ማሰባሰብና ማሰራጨት እንቅስቃሴ ደካማ እንዲሆን ያደርገዋል።

በዚህ የጥናት ስራ ወቅት፣ በገጠሩ ማህበረሰብ ካለው የህግ እውቀት አናሳነት ባሻገር፣ ሌሎች ከሲቪል ማህበረሰቡ የተነሱ አሳሳቢ ጉዳዮች፣ በሴቶች እና ወጣቶች በኩል ያለው የሴት ልጅ ግርዛትን የማመልከት ፍርሃት እና በህጉ ዙሪያ ያሉ የተለያዩ መዋቅሮችም ፍርድ ላይ ለማድረስ አዳጋች የሚያደርጉ መሆኑን ናቸው። በህጉ ዙሪያ ያለ ትምህርት በቂ የሆነ የባህሪ ለውጥ ማምጣቱ እንዳልታመነበት እና የሸሪኣ ህግ ተከታይነት እና የሱና[19] የግርዛት ስርዓት አሁንም ቢሆን ለህግ ተግባራዊነት እክል የሚፈጥሩ ሆነውም ተገኝተዋል።

# ማጠቃለያዎች እና ማሻሻያዎች

## ማጠቃለያ

- የኢትዮጵያ ወንጀልህግ፣ በየትኛውም እድሜ ላይ በምትገኝ ሴት ልጅ ላይ ግርዛት መፈፀም በህግ የሚያስጠይቅ መሆኑን ይገልፃል። ከባድ [3ኛ ደረጃ /መቁረጥ] ለሆኑ ግርዛቶችደግሞ ቅጣቱ ከፍ ይላል።
- አሁን ያሉ ብሄራዊ ህጎች፣ በህክምና የታገዘ የሴቶች ግርዛትን፣ድንበር ዘለል የሴቶች ግርዛትን እና የድርጊቱን መፈፀም ያላመለከተን የሚቀጡ ድንጋጌዎች የላቸውም። ነገር ግን የወንጀልህጉ እንደነዚህ አይነቶቹን ወንጀሎች ጠቅለል አርጎ ያመለክታል።
- የተወሰኑ እስራቶች ቢወሰኑም የህጉ ተፈፃሚነት በጣም ደካማ የሆነ እና ለፍርድ የሚቀርቡ ክሶችም በጣም ጥቂት ናቸው። ወደፍርድ በተወሰዱ ክሶች እና በውጤታቸው ላይ ያሉም መረጃዎች ለህዝብ ተደራሽነታቸው በጣም አናሳ ነው። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ክሶች የሚፈቱት በአካባቢያዊ ወይም ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ነው።
- ኢትዮጵያ የሴቶችን ግርዛት ለማስቀረት ግልፅ የሆነ ብሄራዊ ንድፍ ስላረቀቀች፣ ብሎም የህዝብ ፈንድ ስላዘጋጀች፣ ህዝቡ ስለጎጂ ባህላዊ ልማድ ያለው ግንዛቤ ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ ነው። ነገር ግን ስለህጉ ወሰን እና ምንነት በብዙ ድርጊቱን ፈፃሚ ማህበረሰቦች ያለው ዕውቀት አሁንም ቢሆን አናሳ ነው።

## ማሻሻያዎች

### *ብሄራዊ ህጎች*

- የወንጀልህጉ በሃገሪቷ የሚከናወኑትን ሁሉንም አይነት የሴት ልጅ ግርዛቶችን በግልፅ እንዲያጠቃልል ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል።
- ህጉ በህክምና የታገዘ የሴቶች ግርዛትን ግልጽ የሆነ ትርጉም በመስጠት፣ የትኛውም አይነት የህክምና ባለሙያ በየትኛውም አካባቢ ላይ ይህንን ድርጊት ቢፈጽም፣ ሊፈጽም ቢሞክር ወይም ቢያግዝ ጠበቅ ያለ ቅጣት ሊከተለው ይገባል።
- ህጉ የሴት ልጅ ግርዛትወንጀልን ለመቅጣት የሚያስፈልገውን ጥንካሬ ለማግኘት እና ችግሩ ምን ያክል ስር የሰደደ መሆኑን ለመረዳት፣ ስለድንበር አቋራጭ የሴቶች ግርዛት የበለጠ መረጃ መሰብሰብ አለበት።
- ህጉ በተለይ ለሴት ልጅ ግርዛት፣ ከዚህ ቀደም ተፈጽሞም እንደሆነ፣ አሁንም እየተፈጸመ ቢሆን አልያም ወደፊት ሊፈጸም ታስቦ ባለበት ሁኔታ፣ ለተገቢው አካል ላላሳወቀ ግለሰብ ቅጣት ማስቀመጥ አለበት።
- ህጉ፣ የግርዛት ተጠቂ የሆኑትን ሴቶች ሁሉ የህግ ከለላ ሊያደርግላቸው ይገባል፤ እንዲሁም ማናቸውም በማህበረሰቡ ግፊት ለግርዛት እንዲስማሙ የሆኑ ሴቶችንም ከተጠያቂነት እና ቅጣት ነፃ ሊያደርጋቸው ይገባል።
- ያልተገረዙ ሴቶች እና ቤተሰቦቻቸው ከማህበረሰቡ ለሚደርስባቸው ዘለፋ እና መገለል ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።
- በወንጀልህጉ ውስጥ የተቀመጡ የገንዘብ ቅጣቶች፣ ከ2004 ጀምሮ የተመዘገበውን የዋጋ ንረት ታሳቢ በማድረግ በድጋሚ ሊታዩ ይገባል።

- ህጎች ለሁሉም የማህበረሰቡ አካላት ተደራሽነት ሊኖራቸው እና በየቋንቋው በግልፅ መረዳት በሚቻልበት ሁኔታ ሊዘጋጁ ይገባል።

### *የህግ አተገባበር*

በኢትዮጵያ፤ በከተማው እና በገጠሩ፣ የህግ እውቀት መጠንና ተግባራዊነቱን ለማሻሻል ያሉ እድሎች ሰፊ ልዩነት ይታይባቸዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ የህጉ ተፈጻሚነትን ለማጠናከር [ለፍትህ አካሉ እና ለፖሊስ አካላት የሚሰጠውን ስልጠና ማሻሻልንም አካቶ]፣ እንዲሁም ህጉን እና ሌሎች ክሶችን ለህዝብ ለማዳረስ ፣ በማህበረሰብ ፕሮጀክቱ ውስጥ ህጉን ማስተማር፣ የበለጠ መጠቃለል ካለበት ከገጠሩ ይልቅ፣ በተለይ በአዲስ አበባ መልካም እድል ያለው ይመስላል።

የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም የሚደረገው ስራ በኢትዮጵያ በሚገኙ ማህበረሰቦችን በእነዚህ ሊጠቅም ይችላል፡-

- የሴት ልጅ ግርዛት ክሶችን በበቂ ሁኔታ በመቆጣጠር እና ሪፖርት በማድረግ ለፖሊሲ አርቃቂዎች፣ ለህግ ተርጓሚ አካል፣ ለፖሊስ፣ ለሲቪል ማህበረሰብ እና ለህጉ ተፈጻሚነት ለሚሰራ አካል ሁሉ ማሳወቅ፣
- በህጉ ዙሪያ ግልጽ፣ ለመረዳት የማያዳግቱ፣ ትክክለኛ መረጃዎችን የሚያስተላልፉ ፀረ-የሴት ልጅ ግርዛት የሆኑ ፕሮግራሞች [የተማረ ቁጥር ዝቅተኛ በሆነበት፣ በህጉ ዙርያ ያሉ መረጃዎች በተለያዩ ሚዲያዎች እና ምንጮች ሊቀርቡ ይገባል።]፣
- ህገወጥ ድርጊቶች ተንሰራፍተው በሚገኙበት፣ ድንበር አቋራጭ የሆኑ ትብብሮችን ማጠናከር ላይ መስራት፣
- የአካባቢ እና የሃይማኖት መሪዎችን በህጉ ዙሪያ የማስተማር፣ እንዲሁም የማህበረሰቡን ሴቶች እና ወጣቶች መጠበቅ ላይ ያላቸውን ጣልቃ ገብነት መጨመር፣
- በህጉ ዙሪያ ለሚገኙ ዳኞች እና የአካባቢው ህግ አስፈጻሚዎችን በቂ ድጋፍ እና ስልጠና መስጠት እና በህጉ የተደነገጉትን ቅጣቶች በስርዓቱ እንዲተገብሩ ማበረታታት፣
- ልዩ ፍርድ ቤቶች በሴት ልጅ ግርዛት ላይ የተፈጸሙ ክሶችን እንደ ራዲዮ ባሉ ሚዲያዎች ላይ ጨምሮ፣ ለሁሉም ቋንቋ ተደራሽነት ባለው መልኩ በግልጽ እንዲያሰፍሩ ማበረታታት፣
- ለተጠቂዎች እና አይን እማኞች ያለውን ድጋፍ እና ጥበቃ መጨመር፣
- ሁሉንም በህጉ ዙሪያ ያሉትን ባለሙያዎች ለማንኛዋም በጎጂ ባህላዊ ስርዓት ተጎጂ ለሆነች ወይም የመሆን እድል ላላት ሴት ምላሽ ለመስጠት ስላላቸው ሃላፊነት ስልጠና መስጠት፣
- በሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች ስለሚያጋጥሙ የተገረዙ ሴቶች ሪፖርት ማቅረብን ግዴታ ማድረግ፣
- አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት፣ ነገር ግን በሌለባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ለጎጂ ባህላዊ ስርዓቶች ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች አስፈላጊውን የጥበቃ እርምጃዎችን ማዘጋጀት [ለምሳሌ፥ አስቸኳይ የስልክ የእርዳታ መስመሮችን መዘርጋት ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ማዘጋጀት]።

# ተጨማሪ I: ዓለም አቀፋዊ እና ክልላዊ ስምምነቶች

| ኢትዮጵያ | የተፈረመ | የጸደቀ | የተስማሙ (ስምምነቶች) | የሪፖርቶች ቁጥብነት? |
|---|---|---|---|---|
| **ዓለም አቀፍ** | | | | |
| **የዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኪዳን (ICCPR)** | | | ✓ 1993 | |
| **አለም አቀፍ የኢኮኖሚ, የማህበራዊ እና የባህል መብቶች ኪዳን (1966) (ICESCR)** | | | ✓ 1993 | |
| **በሴቶች ላይ የሚደረጉ ማናቸውም መድሎዎችን ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት (1979) (ሴዳው- CEDAW)** | ✓ 1980 | ✓ 1981 | | በፅሁፍ 29 አንቀፅ 1 የተገደቡ ናቸው ተብሎ አይታሰብም |
| **የስቃይ ቅጣት እና ሌሎች ጨካኝ፣ ኢ፡ሰብዓዊ አያያዝ ወይም ቅጣትን ለመቃወም የተደረገ ስምምነት (1984) (ሲ ቲ ኦ ሲ ዲ ት ፒ - CTOCIDTP)** | | | ✓ 1994 | |
| **የሕፃናት መብቶች ስምምነት (1989) (ሲ ኣር ሲ - CRC)** | | | ✓ 1991 | |
| **አህጉራዊ** | | | | |
| **የአፍሪካ የሰብአዊ እና የህዝቦች መብቶች (1981) (ACHPR) (ባንጁል ቻርተር)** | | ✓ 1998 | | |
| **የአፍሪካ ቻርተር የህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር (1990) (ACRWC)** | | ✓ 2000 | | |
| **የአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች እና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር በአፍሪካ የሴቶች መብት መብቶች (2003) (ACHPRRWA) (ማፑቶ ፕሮቶኮል)** | ✓ 2004 | | | |

**'የተፈረመ'**: ስለ ይዘቱ ከሚደረግ ድርድር እና ስምምነት በኋላ በሃገሮች መካከል የሚፈፀም ውል ነው

**'የጸደቀ'**: አብዛኛዎቹ ዉሎችና ስምምነቶች ከተፈረሙ በኋላ በእዛ ሀገር ህጋዊ ሆኖ እንዲሰራ መፅደቅ አለበት (ማለትም መደበኛ በሆነው የሃገሪቷ የህግ አወጣጥ ስርአት ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል)

**'ስምምነቶች'**: አንድ ሃገር ሌሎች ሀገራቶች የተደራደሩበትን ውል ሲያፀድቅ

1 Federal Democratic Republic of Ethiopia (1995) *Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia* Available at http://www.refworld.org/docid/3ae6b5a84.html.
In Amharic : https://chilot.me/2011/04/ethiopian-constitutions/.

2 Tsegaye Regassa (2004) *State Constitutions in Federal Ethiopia: A Preliminary Observation (A Summary for the Bellagio Conference, March 22-27, 2004).* Available at https://www.researchgate.net/publication/258152597_State_constitutions_in_federal_Ethiopia.

3 *The Revised Constitution of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State* (2001) Available at https://chilot.me/wp-content/uploads/2012/02/southern-nations-nationalities-and-peoples-national-state-constitution-eng.pdf.

4 *Ethiopia: Criminal Code, Proclamation No. 414/2004* (2005) Available at http://www.refworld.org/docid/49216b572.html.
In Amharic: http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/new%20criminal%20code.pdf.

5 *Ethiopian Civil Code* (1930) Available at https://www.trans-lex.org/604600/_/ethiopian-civil-code/.
In Amharic: https://chilot.me/federal-laws/civil-code-amharic/.

6 Central Statistical Agency (CSA) [Ethiopia] and ICF (2016) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2016*, p.325. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland: CSA and ICF. Available at https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR328/FR328.pdf.

7 28 Too Many (2013) *Country Profile: FGM in Ethiopia*, p.38. Available at https://www.28toomany.org/static/media/uploads/Country%20Research%20and%20Resources/Ethiopia/ethiopia_country_profile_v1_(october_2013).pdf.

8 *As at 23 May 2018 (https://www.xe.com/currencyconverter/convert/?Amount=500&From=ETB&To=USD ).*

9 28 Too Many, *op. cit.*, p.55.

10 UNFPA-UNICEF Joint Programme on Female Genital Mutilation/Cutting: Accelerating Change (2015) *2015 Annual Report*, p.21. Available at https://www.unfpa.org/sites/default/files/pub-pdf/UNFPA_FGM_WEB_FINAL_ENGLISH.pdf.

11 *Ibid*, p.36.

12 Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Women, Children and Youth Affairs (MoWCYA) (2013) *National Strategy and Action Plan on Harmful Traditional Practices (HTPs) against Women and Children in Ethiopia*. Available at http://www.africanchildinfo.net/clr/policy%20per%20country/2015%20Update/Ethiopia/ethiopia_htp_2013_en.pdf.

13 UNFPA-UNICEF Joint Programme on Female Genital Mutilation/Cutting: Accelerating Change, *op. cit.,* p.35.

14 Wossen Mulatu (2015) 'Ethiopia, 25 June 2015: Efforts boosted to end child marriage and FGM/C by 2025 at the National Girl Summit', *UNICEF*. Available at https://www.unicef.org/esaro/5440_eth2015_national-girl-summit.html.

15 UNFPA (2015) *The Maternal Health Thematic Fund – Towards the 2030 Agenda: Leaving no one behind in the drive for maternal health: Annual Report 2015*, p.23. Available at https://www.unfpa.org/sites/default/files/pub-pdf/2015_MHTF_Annual_Report-FINAL-web.pdf.

16 *See https://www.28toomany.org/ethiopia/.*

17 Kirrily Pells and Lorriann Robinson (2014) 'Criminalisation will not stop FGM in east Africa', *The Guardian*, 16 April. Available at https://www.theguardian.com/global-development-professionals-network/2014/apr/15/fgm-africa-criminalisation-ethiopia.

18 Central Intelligence Agency (2018) *the World Factbook: Ethiopia*, 13 June. Available at https://www.cia.gov/library/publications/the-world-factbook/geos/et.html.

19 ሱና ማለት መንገድ ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው የመሀመድን ባህሎች እና ብዙ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሱና ብለው የሚያምኑት አነስ ያለ ጉዳት ያለውን የሴት ልጅ ግርዛት አይነትን እንደሆነ ነው(ደረጃ 3 ያልሆነውን)። ነገር ግን በእስልምና ህግ የሱና ባህሎችና ልምዶች አስፈላጊ አደሉም።

**የሽፋኑ ምስል**: Rod Waddington (2014) *Sisters, Wollaita, Ethiopia.* Available at https://flic.kr/p/paEjCD. CCL: https://creativecommons.org/licenses/by-sa/2.0/.

**እዚህ ህትመት ላይ የሰፈሩ የየትኛዋም ሴት ፎቶ ስለ እሷ መገረዝ ወይም አለመገረዝ የሚገልፀው ነገር የለም።**

አብዛኞቹ 'ፌሜል ጄኒታል ሚዩቲሌሽን' የሚሉት መገለጫዎች በጊዜ የመጡ ሲሆኑ፣ ስለልማዱ የተለየ አመለካከትን ይወክላሉ። መገለጫውን ማቆም እና ለወጣት ሴቶች ከለላ ማድረግ የቋንቋ እና የፍቺ ልዩነቶችን ያካትታል።

የተባበሩት መንግስታት ኢንተርኤንጀንሲ 'ኤፍ.ጂ.ኤም'ን በማስቀረት ላይ ያለው ሃሳብ፣ የአለም ጤና ድርጅት 2008ኤ

ክፍል 1፡- አገላለጽ ላይ ማስታወሻ

' 'ሚዩቲሌሽን' የሚለው ቃል ድርጊቱ የሴቶች መብት ጥሰት መሆኑን ያጠናክራል፤ በዚህም በብሄራዊ እና አለም አቀፍ ደረጃ ላለው የማስቆም እንቅስቃሴ ድጋፍ ይሰጣል።'

የተባበሩት መንግስታት የመረብ ላይ በጎ ፈቃደኞቻችን፣ ረዊና ተፈሪ ሓጎስ [Rewina Teferi Hagos] እና ዶክተር ሠምሃል ተፈሪ ሓጎስ [Dr. Semhal Teferi Hagos] ፣ይህንን ህትመት ስለተረጎሙልን/ስላረቀቁልን እናመሰግናለን።, as well as Meron Hailu.

We also would like to thank Yonas Adimassu and his colleagues, from BYA Law Office, for their contribution to the translation of this file, as well as the organisation a4id (Advocates for International Development).

ይህ ሪፖርት የተዘጋጀው ከትረስት ሎው (Trust law) ፣ ቶማስ ሩተርስ ፋውንዴሽንስ ግልባል (The Thomson Reuters Foundation's global) ፣ የህግ ኩባንያዎች እና ቡድኖችን ከመንግስታዊ ያልሆኑ ግብረሰናይ ድርጅቶች (NGOs) ጋር ለማገናኘት አገልገሎት ከሚሰጥ ህጋዊ ነጻ የህግ አገልግሎት (legal pro bono) እና ማህበረሰባዊ እናአካባቢያዊ ለውጥ ለማምጣት ከሚሰሩ ማህበራዊ የንግድ ድርጅት ጋር በመተባበር የተሰራ ነው።

** እዚህ ሪፖርት ላይ የተሰባሰበው መረጃ ከሸርማን እና ስተርሊንግ አል.ኤል.ፒ (Shearman & Sterling LLP) ጋር በመተባበር ለማህበረሰቡ ይፋ ከሆኑ ሰነዶች ሲሆን፣ አገልግሎቱም ለጠቅላላ መረጃነት ብቻ ነው። የተዘጋጀውም ለህጋዊ ጥናት ብቻ ነው እንጂ፤ በማንኛውም የኢትዮጵያ ህግ ላይ ተመስርቶ ምንም አይነት ህጋዊ ምክርን ለመስጠት አይደለም። ምንም አይነት የተሟላ የሆነን፣ ወይም እውነተኛ፣ ወይም ህጋዊ ክስተትን አይወክልም። ህጋዊ ምክርን በምንም አይነት መልኩ አያጠቃልልም፤ እንደዛም ተወስዶ ሊሰራበት፣ ብሎም ከማንኛውም ሰው ወይም ነገር ጋር የጠበቃ-ደንበኛ ግንኙነት ሊፈጠርበት አይገባም። 28 ቱ ሜኒም (28 Too Many) ሆነ ሸርማን እና ስተርሊንግ አል.ኤል.ፒ፣ እንዲሁም ቶምሰን ሮይተርስ ፋውንዴሽንም ሆነ ማንኛውም የሪፖርቱ ተሳታፊ፣ በዚህ ውስጥ ተጠቃሎ በሚገኘው መረጃ ወይም ስህተተኛነት፣ እንዲሁም ከጥናቱ በሰኔ 2018 መጠናቀቅ በኋላ በኖሩ የህግ ለውጦች ላይ ተመስርቶ ለሚመጡ ጉዳዮች ሃላፊነት አይወስዱም። ማንኛውም ለጥናቱ ያበረከተ አካል፣ በጥናቱ ላይ በመሳተፉ ወይም በማበርከቱ ምክኒያት ምክር ለመስጠት ብቁ የሆነ ህጋዊ ስልጣን የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል። ህጋዊ ምክር እንዳስፈላጊነቱ መወሰድ ያለበት ህጋዊ ስልጣን ካላቸው የህግ ባለሙያዎች ነው። ብሎም፣ በአብዛኛው ሀገራት ህጎች ላይ ለሰፈሩት ቅጣቶች ለህጋዊነቱ ቅድሚያ አይሰጡም፤ ማለትም በተግባር ቅጣቶች አነስተኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሊታወቅ ይገባል።

***ምስጋና (Acknowledgements):***
Shearman & Sterling LLP
Girl Generation Ethiopia
Mesfin Tafesse & Associates

**© Orchid Project & 28 Too Many 2018**
*Version 2, 2023*
research@orchidproject.org